# የእርሶ ውሂብ
# የእርሶ መብቶች

*ይህ ማጀት (pantry)ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ የሚገቡበትን ስርዓት ወደ ኤሌክትሮኒክስ ስርዓት በመቀየር ላይ ነው። ይህ ማለት ቀደም ሲል በወረቀት ላይ ይሰበሰቡ የነበሩ ሁሉም መረጃዎች አሁን በኮምፒዩተር አሰራር ስርዓት ተይዘው ይቀመጣሉ ማለት ነው። ይህ ለዚህ ማጀት (pantry)፣ ለ የምግብ ባንኩ (the Food Bank)፣ እና ከሁሉም በላይ ለእርስዎ ትልቅ ለውጥ ነው! ከዚህ በታች የእርስዎን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረናል። ይበልጥ ማወቅ ከፈለጉ፣ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ማጀት (pantry) ውስጥ ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር እባክዎን ይወያዩ።*

## ለውጡ ለምን አስፈለገ?

ይህ ማጀት (pantry) ደንበኞች ከማጀቱ አገልግሎት ለማግኘት የሚመዘገቡበትን አሰራር ሂደት ለማቃለል ከ Capital Area Food Bank ጋር እየሰራ ነው። ስለ እራስዎ እና ስለ ቤተሰብዎ ጥቂት ጥያቄዎችን በመመለስ፣ ከዚህ ማጀት (pantry) አገልግሎት ለማግኘት ይወስድ የነበረ የጥበቃ ጊዜ ወደፊት እንዲቀንስ እና ለእርስዎ የሚሰጡትን አገልግሎቶች ለማሻሻል ይረዳሉ።

## አዲሱ ስርዓት ምንድን ነው?

ስርዓቱ **የአገልግሎት ዕይታዎች** (**Service Insights**) ተብሎ ይጠራል። **ማጀቶች (pantries) ማህበረሰባቸውን በቀላሉ እንዲገነዘቡ/እንዲያውቁ እና አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያስችል የዲጂታል አሰራር ስርዓት ነው።**

መረጃዎን ከሰጡ በኋላ ያመለከቱበት ማጀት (pantry) የአሞሌኮድ (barcode) ካርድ ይሰጥዎታል። **ይህ ማጀት (pantry) (እና የአገልግሎት ዕይታዎችን (Service Insights) የሚጠቀም ማንኛውም ሌላ ማጀት) በበታው መገኘትዎን በፍጥነት መዝግቦ ለማስቀመጥ ይህንን ካርድ ስካን ሊያደርጉ ይችላሉ።** ካርዱ ገንዘብ ያለው ዓይነት ዋጋ የለውም፣ እንዲሁም የቱንም ያህል ማጀቶች (pantries) ቢጎበኙ የሚስፈልግዎት አንድ ካርድ ብቻ ነው።

የምግብ ማጀት ቡድን አባል እንደ ስምዎ፣ እድሜዎ፣ ስልክ ቁጥርዎ፣ የቤተሰብዎ አባላት እድሜን እና የአመጋገብ ምርጫዎችዎ ያሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃል/ትጠይቃለች። እርስዎ አገልግሎቶች እንዳያገኙ ለመከልከል ይህን መረጃ **በፍፁም** ጥቅም ላይ አናውልም፣ እንዲሁም መጎብኘት የሚችሏቸው የማጀቶች ቁጥርን ለመገደብ ዓላማ የአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) መረጃውን **በፍፁም** ጥቅም ላይ አያውልም። የእያንዳንዱ ማጀት የበጎ ፍቃድ አገልጋዮች ማየት የሚችሉት እነርሱ ወደሚያገለግሉበት ማጀት/ድርጅት ብቻ ያደረጉትን የእርስዎን ጉብኝቶች ነው፤ ሌሎች የምግብ ማጀቶችን ከጎበኙ እነዚህን ጉብኝቶች ማየት አይችሉም።

## መረጃዬን ለምንድን ነው የምሰጠው?

አንዳንድ መረጃዎችን በመስጠት፣ የሚከተሉትን ለማድረግ ይረዱናል፡-

- ሰዎች ከማጀቱ ምን ዓይነት ምግቦችን እንደሚፈልጉ ለማወቅ
- ለማጀቱ ገንዘብ ለማሰባሰብ
- አገልግሎት የምንሰጣቸውን ሰዎች ትክክለኛ ቁጥር ለማህበረሰባችን ለማሳወቅ
- የበጎ ፈቃድ አገልጋዮቻችን እርስዎን በማገልገል ብዙ ጊዜ እንዲያሳልፉ እና የወረቀት ስራዎች ላይ የሚያባክኑትን ጊዜ እንዲቀንሱ
- ስለደንበኞቻችን ይበልጥ በመረዳት በተሻለ ለማገልገል

ምግብ ለማግኘት በአገልግሎት ዕይታዎች (Service Insights) ላይ መሳተፍ አይጠበቅብዎትም፣ ነገር ግን ሁሉም ሰው እንዲሳተፍ ይበረታታል።

## ይህን በየግዜው ማድረግ አለብኝ?

አይ የለብዎትም፣ የአገልግሎት ዕይታዎችን በመጠቀም መረጃዎን በኤሌክትሮኒክ መንገድ እንድናከማች እና ወደፊት መረጃዎቹን ስንፈልግ በፍጥነት እንድናገኝ ያስችለናል። በየጊዜው መረጃዎን እንዲያረጋግጡ እና እንዲያሻሽሉ/እንዲያዘምኑ ብቻ እንጠይቅዎታለን።

CAPITAL AREA FOOD BANK

# የእርሶ ውሂብ የእርሶ መብቶች

## የ CAFB ውሂብ ቃልኪዳን

**እርስዎን እና መረጃዎን በማዕረግ እና በአክብሮት እንይዛለን።**

የሚሰጡን ምላሾች በምስጢር ይያዛሉ። የእርስዎን መረጃ መስጠት ካልፈለጉ ወይም መመለስ ምቾት የማይሰጥዎ ማንኛውም ጥያቄ ከቀረበልዎ፣ ምንም ይሁን ምን ለእርስዎ አገልግሎቶችን መስጠታችን አይቀርም። እርስዎ የሚሰጡንን መላሾች አምነን እንቀበላለን፣ እንዲሁም ላለመሳተፍ ከመረጡ ከሌሎች በተለየ መንገድ አንይዘትም።

**የእርስዎን መረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ እና በአስተማማኝ መንገድ እንይዛለን።**

መረጃዎ በይለፍ ቃል ጥበቃ በሚደረግለት ስርዓት ውስጥ ይከማቻል። ከዚህ የአጋር አውታረ መረብ ውጪ ላለ አካል የእርስዎን የተናጠል፣ የግል መረጃ **በጭራሽ** አናጋራም። የእርስዎን የግል መረጃ እንደ ህግ አስከባሪ አካላት ወይም የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ላሉ ኤጀንሲዎች ጋር **በጭራሽ** አናጋራም። የወረቀት ቅበላ ቅፁን ሞልተው ካጠናቀቁ፣ በማጀትዎ ውስጥ ሚሰሩ ሰራተኞች ወረቀቱ እንደማያስፈልጋቸው ሲያረጋግጡ ወዲያው ይቀዳድዱታል።

**ይህንን መረጃ ለእርስዎ የተሻሉ አገልግሎቶችን ለመስጠት ብቻ እንጠቀምበታለን።** መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎን ለእኛ በመስጠት፣ አገልግሎቶቻችን በተቻለን መጠን ከማህበረሰቡ ፍላጎቶች የተጣጣሙ ለማድረግ እንድንችል ይረዱናል። የእርስዎን ግላዊ እንቅስቃሴ ለመከታተል ወይም አገልግሎቶችን ከእርስዎ ለመገደብ ይህንን መረጃ **አን**ጠቀምበትም። የምግብ ባንኩ (The Food Bank) የእርስዎን መረጃ አይሸጥም ወይም ለገበያ ወይም ለንግድ ዓላማ ፈጽሞ አይጠቀምም። የእርስዎን መረጃ የሚከፍት ማንኛውም ሰው ይህን የሚያደርገው አገልግሎቶችን ለመመዝገብ ወይም መግለጫዎን ለማዘመን ብቻ ይሆናል። የእርስዎ ማጀት (pantry) እና የምግብ ባንኩ (the Food Bank) አዝማሚያ/ዝንባሌዎችን ለመለየት እና ስለ ማህበረሰቡ የበለጠ ለማወቅ ሪፖርቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። እነዚህ ሪፖርቶች በግል የእርስዎን ማንነት ለይቶ ሊያሳውቅ የሚችል መረጃን በጭራሽ አያሳዩም።

***ጥያቄዎች ወይም ስጋቶችካልዎት?***

በ *www.capitalareafoodbank.org/insights* *ይጎብኙ ወይም በኢሜይል*
*አድራሻ*ServiceInsights@capitalareafoodbank.org ላይ መልዕክት ይላኩ።